# ስለ ፓክስሎቪድ ማወቅ ያለብዎት

## ፓክስሎቪድ ምንድነው?

ፓክስሎቪድ በኮቪድ-19 እንዳይታመሙ የሚከላከል መድኃኒት ነው።

ኮቪድ-19 በሰውነትዎ ውስጥ እንዳይሠራጭ ለማስቆም በጋራ አብረው የሚሠሩ ሁለት መድኃኒቶችን (nirmatrelvir (ኒርማትሬልቪር) እና ritonavir (ሪቶናቪር)) ይዟል።

ፓክስሎቪድ የሕመም ስሜቶችዎ እንዳይባባሱ ሊያደርግና በኮቪድ-19 ምክንያት ወደ ሆስፒታል የመሄድ ዕድልን ሊቀንስ ይችላል።

**ፓክስሎቪድ በኮቪድ-19 እንደገና ከመያዝ አያግድዎትም።**

**ፓክስሎቪድ የክትባት ምትክ አይደለም። ከከባድ የኮቪድ-19 ኢንፌክሽን በጣም ጥሩው መከላከያ ወቅታዊ ክትባቶችን መውሰድ ነው።**

## ፓክስሎቪድን መውሰድ ያለበት ማነው?

በኮቪድ-19 ምክንያት ለከባድ ሕመም ተጋላጭ ከሆኑ ፓክስሎቪድን መውሰድ ይችላሉ። ፓክስሎቪድ በደንብ እንዲሠራ የሕመም ምልክቶች በጀመሩ በአምስት ቀናት ውስጥ መውሰድ መጀመር አለብዎት።

ለከባድ ሕመም የመጋለጥ ዕድልዎ በጤናዎ፣ ዕድሜዎ እና በክትባትዎ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው።

አንድ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ከፍተኛ አደጋ ላይ ከሆኑ ሊነግርዎት/ልትነግርዎት ይችላል/ትችላለች። በተጨማሪም ከፍተኛ አደጋ ላይ ሊወድቁ እንደሚችሉ ለማወቅ የኦንታሪዮን ማጣሪያ መሳሪያን መጠቀም ይችላሉ፦ **https://covid-19.ontario.ca/covid-treatment-screener**

የሚከተሉት ከሆኑ ከፍ ያለ አደጋ ሊያጋጥምዎት ይችላል፦

- ✓ ዕድሜዎ 60 ወይም ከዛ በላይ፣
- ✓ 18 ወይም ከዛ በላይ እና የሰውነትዎ ከበሽታ የመከላከል አቅም የተዳከመ ከሆነ (በበሽታ ወይም በመድኃኒቶች ምክንያት የሰውነትዎ ከበሽታ መከላከያ ሥርዓት የተዳከመ ከሆነ)፣
- ✓ ከ18 እስከ 59 ዓመት እና የኮቪድ-19 በቂ መከላከያ ከሌልዎት (ለምሳሌ አልተከተቡም ወይም ክትባት ከወሰዱ ወይም ኮቪድ-19 ከያዝዎት ከስድስት ወር በላይ ከሆነ)
- ✓ ከ18 እስከ 59 ዓመት እና ለከባድ ኮቪድ-19 ተጋላጭ የሚያደርጉ አንድ ወይም ከዛ በላይ የጤና እክሎች። ለከባድ ኮቪድ-19 ተጋላጭ የሚያደርጉ አንዳንድ የጤና እክሎች የሚከተሉት ናቸው፦
  - ካንሰር
  - የአንጎልና ደምስሮቹ በሽታ (ለምሳሌ ስትሮክ)
  - የኩላሊት በሽታ
  - የጉበት በሽታ
  - የሳንባ በሽታ
  - ሲስቲክ ፋይብሮሲስ
  - የስኳር በሽታ
  - የአካል/የአእምሮ ጉዳቶች
  - የልብ በሽታዎች
  - የHIV በሽታ
  - አንዳንድ የአእምሮ ጤና በሽታዎች
  - ከመጠን ያለፈ ውፍረት
  - እርግዝና እና በቅርብ ጊዜ የነበረ እርግዝና
  - ማጨስ (የአሁን ወይም የቀድሞ)
  - ነቀርሳ

**በኮቪድ-19 ምክንያት ለከባድ ሕመም የመጋለጥ ስጋት ላይ ነኝ ብለው ካሰቡ ስለ አማራጮች ለመወያየት የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ያነጋግሩ።**

## ኮቪድ-19 የያዘኝ ይመስለኛል። ፓክስሎቪድ የማገኘው እንዴት ነው?

ምልክቶችዎን እዚህ ጋር ማጣራት ይችላሉ፦ **covid-19.ontario.ca/exposed#symptoms**

ለከባድ ሕመም ተጋላጭ ነኝ ብለው ካሰቡና የኮቪድ-19 ምልክቶች ካሉብዎት የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

- መድኃኒት ቤትዎ ጋር መደወል (በርካታ መድኃኒት ቤቶች ፓክስሎቪድን ማዘዝ ይችላሉ)
- ዋና ሕክምና አቅራቢዎ ጋር መደወል (የቤተሰብ ዶክተር ወይም ነርስ ፕራክቲሽነር)

በተጨማሪም ጥያቄ ካልዎት ወይም እርዳታ ካስፈለግዎት Health811 ጋር መደወል ይችላሉ። 811 ይደውሉ ወይም ከነርስ ጋር በኢንተርኔት ለመነጋገር **ontario.ca/health811**ን ይጎብኙ።

ይህ ለእርስዎ የሚሆን ከሆነ Health811 ወደ ምናባዊ እንክብካቤ ምክክር ሊያገናኝዎት ይችላል።

**ምልክቶች እንደጀመሩዎት ወዲያውኑ የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ማነጋገር አስፈላጊ ነው።** ፓክስሎቪድ በደንብ እንዲሠራ ምልክቶች በጀመሩ በአምስት ቀናት ውስጥ መጀመር አለበት።

Ontario Health

ከባድ ምልክቶች ካጋጠሙዎት ወደ 911 ይደውሉ ወይም ወደ ድንገተኛ ክፍል ይሂዱ። ከባድ ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

- የመተንፈስ ችግር
- የደረት ሕመም
- እራስን መሳት
- ግራ መጋባት

## ከሕክምና አቅራቢዬ ጋር ስለ ፓክስሎቪድ በምነጋገርበት ጊዜ ምን ዓይነት መረጃ ማምጣት ይኖርብኛል?

ከሕክምና አቅራቢዎ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ የሚከተሉትን ማምጣት ይኖርብዎታል:-

- የሚወስዷቸውን መድኃኒቶች ዝርዝር በሙሉ፣ ዶክተር ያዘዛቸውንም የዶክተር ትእዛዝ የማያስፈልጋቸውንም፣ ቫይታሚኖችን እና ከእፅዋት የተቀመሙ መድኃኒቶችን ጨምሮ
- የሕመሞችዎን ዝርዝር
- ማንኛውም በቅርብ የተደረገ የደም ምርመራ፣ ማግኘት ከቻሉ

ምንም ዓይነት አለርጂ፣ የጉበት ወይም የኩላሊት በሽታ ወይም ነፍሰ ጡር፣ ጡት እያጠቡ ወይም ባለ ሆርሞን የወሊድ መቆጣጠሪያ (እንደ ወሊድ መቆጣጠሪያ ኪኒን ወይም ተለጣፊ) እየወሰዱ ከሆነ የሕክምና አቅራቢዎን ያሳውቁ።

## ፓክስሎቪድ ለማግኘት የኮቪድ-19 ምርመራ ማድረግ አለብኝ?

ፓክስሎቪድ ለማግኘት ፖዚቲቭ የኮቪድ-19 ምርመራ ውጤት ያስፈልግዎታል። ይህም PCR፣ rapid molecular test (ፈጣን የሞሌክዩል ምርመራ)፣ ወይም rapid antigen test (ፈጣን የአንቲጂን ምርመራ) ሊሆን ይችላል (በቤት ውስጥም የተደረገ ቢሆን)፡፡

**የሕክምና አቅራቢዎን ስለ ፓክስሎቪድ ከማነጋገርዎ በፊት ፖዚቲቭ የምርመራ ውጤት አያስፈልግዎትም።** ካስፈለግዎት ምርመራ እንዲያደርጉ እነሱ ያግዙዎታል።

## ፓክስሎቪድ ነጻ ነው?

ከሕክምና አቅራቢ ትእዛዝ ካለ ፓክስሎቪድ በነጻ ነው የሚገኘው። ፓክስሎቪድ ለማግኘት የOHIP ካርድ አያስፈልግዎትም።

## ፓክስሎቪድን የምወስደው እንዴት ነው?

ፓክስሎቪድ በቀን ሁለት ጊዜ ለአምስት ቀናት በአፍ ይወሰዳል።

ፓክስሎቪድ የጠዋት መጠንና የምሽት መጠን በያዘ ጥቅል ውስጥ ይመጣል። እያንዳንዱ መጠን 2 የnirmatrelvir (ኒርማትሬልቪር) ኪኒኖች (ሮዝ ኪኒኖች) እና 1 የritonavir (ሪቶናቪር) ኪኒን (ነጭ ኪኒን) አለው።

የኩላሊት በሽታ ያለባቸው ሰዎች ዝቅ ያለ መጠን ሊታዘዝላቸው ይችላል።

ሶስቱንም የጠዋት ኪኒኖች በአንድ ላይ እና ሶስቱንም የምሽት ኪኒኖች በአንድ ላይ ለ5 ቀናት ሙሉ መውሰድ አለብዎት። ፓክስሎቪድ ከምግብ ጋር ወይም ያለ ምግብ መወሰድ ይችላል።

አንድ የፓክስሎቪድ ዙር ሳይወስዱ ጊዜው ካለፈብዎትና መውሰድ ከሚገባዎ ጊዜ ከ8 ሰዓት በታች ከሆነ፣ እንዳስታወሱ ወዲያው ይውሰዱት። ዙሩ ካመለጥዎት ከ8 ሰዓት በላይ ከሆነ፣ ይለፉትና የሚቀጥለውን ዙር ሰዓት ጠብቀው ይውሰዱ። 2 የፓክስሎቪድ መጠኖች (6 ኪኒኖች) በአንድ ጊዜ አይውሰዱ።

ፓክስሎቪድን ሁልጊዜ የሕክምና አቅራቢው በነገርዎት መሠረት ይውሰዱ።

**ፓክስሎቪድን በሚወስዱበት ጊዜ በሽታውን ሊያጋቡ ስለሚችሉ ስርጭቱን ለመገደብ የጤና መምሪያ መመሪያዎችን ይከተሉ።** ስለ ወቅታዊ የጤና መምሪያ መመሪያዎች እዚህ ያንብቡ:- **https://www.ontario.ca/page/public-health-measures-and-advice**

## የፓክስሎቪድ ተያያዥ ችግሮች ምንድን ናቸው?

ፓክስሎቪድ በሚወስዱበት ጊዜ የሚከተሉት ተያያዥ ችግሮች ሊያጋጥሙዎት ይችላሉ:-

- የጣዕም መቀየር
- ተቅማጥ
- ከፍተኛ ደም ግፊት
- የጡንቻ ሕመም
- የሆድ ሕመም
- ማቅለሽለሽ
- ባጠቃላይ ጤና ማጣት

ሌሎች ተያያዥ ችግሮች ሊያስተውሉ ይችላሉ። የሚያስቸግሩዎት ወይም የማይጠፉ ተያያዥ ችግሮች ካሉዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

ሌሎች ያልተለመዱ ሆኖም ሊከሰቱ የሚችሉ የፓክስሎቪድ ተያያዥ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፦

- **የአለርጂ ምላሾች።** የአለርጂ ምላሽ ከሆኑት ከሚከተሉት የአለርጂ ምልክቶች አንዱ ካጋጠምዎት ፓክስሎቪድ መውሰድ ያቁሙና የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይደውሉ፦ ቆዳዎ ላይ የሚያሳክኩ ቦታዎች (እብጠቶች)፣ የመዋጥ ወይም የመተንፈስ ችግር፣ የከንፈር፣ የፊት ወይም የምላስ እብጠት፣ የጉሮሮ መጥበብ ወይም መጎርነን።
- **የጉበት ችግሮች።** ከሚከተሉት የጉበት ችግር ምልክቶች አንዱ ካልዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ወዲያው ያሳውቁ፦ ቢጫማ ቆዳ ወይም ዓይን (ጃንዲስ)፣ ያልተለመደ ጠቆር ያለ ሽንት፣ በሆድዎ በቀኝ በኩል አዲስ ሕመም።
- **የኤችአይቪ መድኃኒቶች እንዳይሠሩ ማድረግ።** ሕክምና ያልተደረገለት የኤችአይቪ ኢንፌክሽን ካለብዎት፣ ፓክስሎቪድ አንዳንድ የኤችአይቪ መድኃኒቶችን ወደፊት በደንብ እንዳይሠሩ ሊያደርግ ይችላል።

## ሌሎች መድኃኒቶችን እየወሰድኩ ፓክስሎቪድንም መውሰድ እችላለሁ?

ፓክስሎቪድ ብዙ በብዛት ጥቅም ላይ ከሚውሉ መድኃኒቶችና ማሟያዎች ጋር አብሮ መሥራት ይችላል። ፓክስሎቪድን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መውሰድ እንዲችሉ አንድ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ (ለምሳሌ ፋርማሲስት) ሌሎቹ መድኃኒቶችዎ ላይ ለውጥ ሊያደርግ/ልታደርግ ይችላል/ትችላለች።

በተጨማሪም ፓክስሎቪድ በሆርሞን የሚሠሩ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል። ፓክስሎቪድ በሚወስዱበት ጊዜ ሌላ ዓይነት የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም አለብዎት (ለምሳሌ ኮንዶም ወይም መቆጠብ)።

## የኮቪድ-19 ምልክቶቼ ከተባባሱ ምን ማድረግ ይገባኛል?

ካልተሻልዎት ወይም ከ5 ቀናት በኋላ ከባሰብዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

ከባድ ምልክቶች ከታዩ ወደ 911 ይደውሉ ወይም ወደ ድንገተኛ ክፍል ይሂዱ። ከባድ ምልክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- የመተንፈስ ችግር
- የደረት ሕመም
- ራስን መሳት
- ግራ መጋባት

ይህ መረጃ ከጃኑዋሪ 2023 ጀምሮ ትክክለኛ ነው።

**ይህን መረጃ ተደራሽ በሆነ ቅርጸት ይፈልጋሉ?**
1-877-280-8538፣ TTY 1-800-855-0511፣ info@ontariohealth.ca

Publication No. 301212 (Amharic)
ISBN No. 978-1-4868-6843-8 (PDF)
© King’s Printer for Ontario, 2023